# DHSP የሕጻናት ክብካቤ እና የቤተሰብ ድጋፍ
# ቅድመ ትምህርት ቤት ሎተሪ
# በብዛት የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**ወደ DHSP ቅድመ ትምህርት ቤት ሎተሪ ለመግባት መስፈርቱን የሚያሟላው ማነው?**

የካምብሪጅ ነዋሪዎች ሆነው በዕድሜያቸው መስፈርቱን የሚያሟሉ ልጆች ያሏቸው ወደ DHSP ቅድመ ትምህርት ቤት ሎተሪ መካተት ይችላሉ። በ2010-2021 የትምህርት ዘመን ለመምዝገብ ለሚወጣው የ 2019 ሎተሪ፣ ከኤፕሪል 1፣ 2016 - ጃንዋሪ 1፣ 2018 የተወለዱ ልጆች በዕድሜያቸው መስፈርቱን እንደሚያሟሉ ይቆጠራል።

**በDHSP ሎተሪ ውስጥ እንዴት መካተት እችላለሁ?**

ለቀጣዩ የትምህርት ዘመን የሎተሪ ማመልከቻዎችን ኦክቶበር ውስጥ እንቀበላለን። ለጅዎ ለቅድመ ትምህርት ቤት ተሳትፎ የዕድሜ መስፈርቱን የሚያሟላው/የምታሟላው የ2 ዓመት 9 ወር – 4 ዓመት 5 ወር መካከል ከሆነ/ች ነው። **ለምሳሌ፣ በኦክቶበር 2019 በሎተሪው ለመካተት (ለ2010-2021 የትምህርት ዘመን ለመመዝገብ)፣ የልጅዎ የልደት ቀን በኤፕሪል 1፣ 2016 - ጃኑዋሪ 1፣ 2018 መካከል መሆን አለበት።**

የሎተሪ ማመልከቻዎ የተሟላ እንደሆነ እንዲቆጠር፣ የሚከተሉትን ሰነዶች ማያያዝ አለብዎ፦

- **DHSP ቅድመ ትምህርት ቤት ሎተሪ**
- **የገቢ ማስረጃ እና የቤተሰብ መጠን፦** የግብር ማመልከቻ እና 4 ተከታታይ የክፍያ ካርኒዎች (ወይም ያለፉት 30 ቀናት) ወይም አሁን እየተቀበሏቸው ያሉ ጥቅማጥቅሞች የስጦታ ደብዳቤዎች (TANF፣ SSI፣ SNAP፣ WIC፣ ወዘተ)
- **የልጁ ዕድሜ ማስረጃ፦** የልጁ የልደት ሰርቲፊኬት ወይም የልጁ ፓስፖርት
- **የአድራሻ ማረጋገጫ፦** ሊዝ፣ ሞርጌጅ፣ ከመኖሪያ ቤት አቅራቢ የተሰጠ ደብዳቤ፣ ባለፉት 2 ወራት ውስጥ የተከፈለ የፍጆታ ደረሰኝ፣ ወይም ደብሊንግ አፕ ቅጽ

**ለ DHSP ቅድመ ትምህርት ቤት ሎተሪ ማመልከቻውን ከየት አገኛለሁ?**

የDHSP ቅድመ ትምህርት ቤት ሎተሪ ማመልከቻዎች በሚከተሉት አካባቢዎች ይገኛሉ፦

- cambridgema.gov/DHSP
- finditcambridge.org
- DHSP፦ 51 Inman St., 3rd floor, Cambridge, MA 02139
- Center for Families: 70 Rindge Ave. (ከሕንጻው ጀርባ)፣ Cambridge, MA 02140
- ካምብሪጅ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ምዝገባ ማዕከል፦ 459 Broadway, Cambridge, MA 02138

**ለ DHSP ቅድመ ትምህርት ቤት ሎተሪ ማመልከቻውን የት ማስገባት እችላለሁ?**

ኦክቶበር ውስጥ፣ ማመልከቻዎን እና ደጋፊ ሰነዶችዎን ወደሚከተሉት አድራሻዎች በእጅ መስጠት ይችላሉ፦

- DHSP፦ 51 Inman St., 3rd floor, Cambridge, MA 02139
- Center for Families: 70 Rindge Ave. (ከሕንጻው ጀርባ)፣ Cambridge, MA 02140

- ካምብሪጅ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ምዝገባ ማዕከል፡- 459 Broadway, Cambridge, MA 02138

በደጋፊ ሰነዶቹ ውስጥ ብሚካተቱ ምስጢራዊ መረጃዎች ምክንያት የቅድመ ትምህርት ቤት ሎተሪ ማመልከቻዎችን በኤሌክትሮኒክ ዘዴ መቀበል አንችልም።

**በDHSP ቅድመ ትምህርት ቤት ውስጥ ቦታ ለማግኘት ያለኝን ዕድል እንዴት ማስፋት እችላለሁ?**

በርካታ ፕሮግራሞችን ከመረጡ ቦታ የማግኘት ዕድልዎ ይሰፋል። በሰዓቶች ወይም በአካባቢ ምክንያት ልጅዎን ሊልኩባቸው የማይችሏቸው ማናቸውም ፕሮግራሞች ካሉ፣ እባክዎ አይምረጧቸው። ልጅዎን ሊልኩ በማይችሉበት ፕሮግራም ውስጥ ላለ ቦታ ቢመረጡ፣ ቦታውን በፈቃድዎ እንደተዉ ይቆጠርና ለሌሎች የመረጧቸው ፕሮግራሞች በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ይመዘገባሉ።

**ልጄ በDHSP ቅድመ ትምህርት ቤት ውስጥ ቦታ ማግኘቱን/ቷን ማወቅ የምችለው መቼ ነው?**

ከሎተሪው በኋላ ዲሴምበር ውስጥ ያውቃሉ።

**በDHSP ውስጥ ቦታ ቢሰጠኝ፣ ልጄን በፕሮግራሙ ውስጥ ማስመዝገብ እንደምፈልግ ማረጋገጫ መስጠት ይኖርብኛል?**

አዎ። ሁሉም ቦታ የተሰጣቸው ቤተሰቦች እስከ ጃንዋሪ 31 ድረስ የተሰጣቸውን ቦታ መቀበላቸውን ወይም አለመቀበላቸውን እንዲያረጋግጡ ይጠየቃሉ። ከአንድ ቤተሰብ እስከ ጃኑዋሪ 31 ድረስ ምላሽ ካላገኘን፣ ቦታውን በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ላለ ሌላ ልጅ እንሰጣለን።

**በ2019-2020 የትምህርት ዘመን የመንፈቅ-ዓመት ክፍት ቦታዎችን እንዴት ትሞላላችሁ?**

ማናቸውም በ2019-2020 የትምህርት ዘመን የሚኖሩ ክፍት ቦታዎች ለ2020-2021 የትምህርት ዘመን በተመረጡ የዕድሜ መስፈርቱን የሚያሟሉ ልጆች ይሞላል። ከዚያም እንደ አስፈላጊነቱ፣ የ2020-2021 የትምህርት ዘመን ክፍት ቦታዎችን ለመሙላት ለ2019-2020 ክፍት ቦታዎችን ለመሙላት ከተፈጠረው የአጭር ጊዜ ተጠባባቂዎች ዝርዝር ልጆችን እናስገባለን።

**በDHSP የቅድመ ትምህርት ቤት ሎተሪ ውስጥ የእህትና ወንድም ምርጫ ይኖራል?**

ሎተሪው በሚከናወንበት ተመሳሳይ ጊዜ ከቅድመ ትምህርት ቤት ፕሮግራሞቻችን ውስጥ እህት ወይም ወይም ወንድም ያላቸው ልጆች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።

**የካምብሪጅ ነዋሪ ባልሆንም የካምብሪጅ ከተማ ወይም የካምብሪጅ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሰራተኛ ብሆን ልጄን በDHSP ቅድመ ትምህርት ቤት ሎተሪ ውስጥ ማካተት እችላለሁ?**

እንደ ሁልጊዜው፣ የካምብሪጅ ነዋሪዎች በዋነኛነት ቅድሚያ የምንሰጣቸው ናቸው። ለ2020-2021 የትምህርት ዘመን ምዝገባ ለ2019 ሎተሪ፣ የካምብሪጅ ነዋሪዎች ያልሆኑ የካምብሪጅ ከተማ እና የካምብሪጅ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሰራተኞች ሎተሪው ውስጥ መካተት ይችላሉ። የካምብሪጅ ነዋሪዎች ላልሆኑ የካምብሪጅ ከተማ እና የካምብሪጅ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሰራተኞችን ችሎታ በየዓመቱ ከሎተሪው በፊት እንደገና እንገመግማለን። በአድራሻ ማረጋገጫ ሰነድ ምትክ፣ የካምብሪጅ ከተማ እና ካምብሪጅ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሰራተኞች የቅጥር ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው።

### ከDHSP ሎተሪ ወደ ተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ከገባሁ ምን አደጋለሁ?

ክፍት ቦታዎች በሚገኙ ጊዜ፣ ክፍት ቦታውን ለመስጠት በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ላሉ ቤተሰቦች ስልክ እንደውላለን። የተጠባባቂ ዝርዝሩ ለሚቀጥለው ሎተሪ ተሳታፊዎችን መቀበል እስከምንጀምር (የሚቀጥለው ዓመት ኦክቶበር) ድረስ ይቆያል። በቀጣዩ ዓመት ኦክቶበር ውስጥ፣ የተጠባባቂ ዝርዝሩ ጊዜው ያበቃል እናም ልጆቻቸው አሁንም የዕድሜ መስፈርቱን የሚያሟሉ ቤተሰቦች ለቀጣዩ ዓመት ምዝገባ እንደገና በሎተሪው ውስጥ እንዲሳተፉ ይበረታታሉ።

ተለዋጭ ፕሮግራም ለማግኘት እገዛ የሚፈልጉ ከሆነ፣ ቅድመ ትምህርት ቤቶችን ለማግኘት የሚከተሉት የመረጃ ምንጮች አሉ፡-

- Find It Cambridge፡- finditcambridge.org ወይም 617-652-5232
- Birth to 3rd Partnership: cpsd.us/departments/b3 ወይም 617-349-6554
- Department of Early Education and Care: eeclead.force.com/EEC_ChildCareSearch
- Center for Families: 617-349-6385

### የDHSP ትምህርት ቤቶች ለመማር ምን ያህል ያስከፍላል?

DHSP ቅድመ ትምህርት ቤት የክፍያ ተመኖች በገቢ ላይ የተመሰረተ ተንሸራታች ልኬት ያላቸው ናቸው። ተመኑ በየዓመቱ በDHSP የቅድመ ትምህርት ቤት ሎተሪ መረጃ መስጫዎች ላይ ይለቀቃል

በሰብዓዊ አገልግሎት ፕሮግራሞች መምሪያ ውስጥ፣ ፕሮግራሞቻችን ለሁሉም የካምብሪጅ ቤተሰቦች ተደራሽ እንዲሆን ይንጥራለን። ቅድመ ክፍያ ካርዶችን እንቀበላለን እንዲሁም መስፈርቱን ለሚያሟሉ ቤተሰቦች ጉልህ የትምህርት ክፍያ እገዛ እናደርጋለን። አንድ ቤተሰብ የሚቀበለው የትምህርት ክፍያ እገዛ በአጠቃላይ የቤተሰብ ገቢ፣ የቤተሰብ መጠን፣ እና የግል ኑሮ ክብደት ላይ የተመሰረተ ነው።

ለ2020 - 2021 የትምህርት ዘመን የትምህርት ክፍያ ተመኖቻችን የሚከተሉት ናቸው፡-

| አጠቃላይ የቤተሰብ ገቢ | የትምህርት ክፍያ ተመን በቀን | የትምህርት ክፍያ ተመን በሳምንት | አማካይ ተመን በወር** |
|---|---|---|---|
| $204,001 – በላይ | $78.46 | $392.30 | $1,726.12* |
| $153,001- $204,000 | $62.77 | $313.85 | $1,380.94* |
| $122,401- $153,000 | $47.08 | $235.40 | $1,035.76* |
| $102,001– $122,400 | $37.66 | $188.30 | $828.52* |

| | | | |
|---|---|---|---|
| $0- $102,000 | መነሻ ዕለታዊ ተመኑ $37.66 ነው። አጠቃላይ የቤተሰብ ገቢያቸው $0 - $102,000 የሆኑ ቤተሰቦች ለትወሰነ የትምህርት ክፍያ መስፈርቱን ያሟላሉ። አንድ ቤተሰብ የሚቀበለው የትምህርት ክፍያ እገዛ በአጠቃላይ የቤተሰብ ገቢ፣ የቤተሰብ መጠን፣ እና የግል ኑሮ ክብደት ላይ የተመሰረተ ነው። | | |

*በእያንዳንዱ ወር ውስጥ ባለው ክፍያ ሊጠየቅባቸው የሚችሉ ቀናት መሰረት ወርሃዊ ተመንኡ ከወር ወደ ወር ሊለያይ ይችላል። ወርሃዊ አማካይ ተመን የሚሰላው 22 ክፍያ ሊጠየቅባችው የሚችሉ ቀናት ላይ ተመስርቶ ነው።

## ለስኮላርሺፕ እንዴት ማመልከት ችላለሁ?

ተጨማሪ ወረቀት መሙላት አያስፈልግዎትም! የትምህርት ክፍያ ድጋፍን ጨምሮ የትምህርት ክፍያ ተመንዎን ለማስላት በሎተሪው ለመካተት ያስገቧቸውን ሰነዶች እንጠቀማለን።

## ከፍተኛውን ተመን የምከፍል ከሆነ፣ የገቢ ማስረጃ እና የቤተሰብ መጠን ማረጋገጫ ማቅረብ ይጠበቅብኛል?

ገቢዎ በከፍተኛው ክልል ውስጥ የሚወድቅ ከሆነ፣ የገቢ ወይም የቤተሰብ መጠን ማስረጃ ማቅረብ አይጠበቅብዎትም። ነገር ግን አሁንም ቢሆን የልጅዎን ዕድሜ እና አድራሻ ማረጋገጥ ይኖርብዎታል።

## የDHSP ቅድመ ትህምርት ቤት የሥራ ሰዓቶች የትኞቹ ናቸው?

ሁሉም የDHSP ቅድመ ትምህርት ቤቶች በዓመት ለ12 ወራት እና በሳምንት 5 ቀናት (ከሰኞ - ዓርብ) ይሰራሉ። The Haggerty, Kennedy/Longfellow, M.L. King እና Windsor Preschools ከ7:30 a.m. – 5:30 p.m. ይሰራሉ፣ The King Open፣ Morse፣ እና Peabody ቅድመ ትምህርት ቤቶች ከ 8:00 a.m. – 6:00 p.m. ይሰራሉ።

## በDHSP ውስጥ ከሥራ ሰዓት ውጭ የሚሰቱ ባዶ ቦታዎች ይኖራሉ?

በማናቸውም ፕሮግራማችን ውስጥ ከሥራ ሰዓት ውጭ የሚሰጡ ፕሮግራሞች አንሰጥም። ሁሉም ቦታዎች በሳምንት ለ5 ቀናት እና በዓመት ለ12 ወራት ናቸው።